# <u>ድር ቢያብር አንበሳ ያስር</u>

## <u>ከጋሻ ለኢትዮጵያውያን የተሰጠ መግለጫ</u>

ሰሞኑን በመድረክና ሌሎች ተቃዋሚ ሀይሎች አማካኝነት በመላው ኢትዮጵያ በተለይም የህወሓት መሰረት እየተባለ ሲጠራ በቆየው ትግራይ የሚታየው አበራታች ክስተት የአንድነት ስራ እንቅስቃሴ ውጤት ለመሆኑ ለማንም ግልፅ ነው። ይህ የሚታየው ተስፋ የተገኘው የረጅም ጊዜ የጭቆና ውጤት ነውና የተከፈለውም መስዋእትነት ግን ቀላል አለመኖሩ ሁላችንም የተከታተልነው ጉዳይ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን ከምርጫ 97 በኃላ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ብቅ ብለው በነበሩበት ወቅት በደምስ በለጠ አዘጋጅነት አቦጊዳ ተብሎ ይጠራ በነበረው የረዲዮ ፕሮግራም ቃለ-መጠይቅ ተደርጎላቸዋል። በዚሁ ፕሮግራም ከአድማጭ የሚከተልው ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። በውጭ ከሚገኙት የትግራይ ተወላጅ ወንድሞቻችን መቃቃር አለ፡ አገር ቤት ውስጥስ ሁኔታው እንዴት ነው? ሲመልሱም "አዲስ አበባ የሚገኘው የመረጠው ቅንጅትን ነው። "በትግራይ የሚኖረው ግን ነፃ እንዳወጣን ሁሉ ነፃ የምናወጣው እኛ ነን።" "ሆኖም እነሱም መታገል አለባቸው" ባሉበት ወቅት ስለ ጭቆናው ብዛት ሲያብራሩ ምሳሌ ሰጥተው ነበር። አንዴ በመቀሌ የኢድዩ አባል ባሉት ሰው ከብዙ ግርፋት በኃላ በከተማው እያዞሩት ነበር ያዋሉት። በዚሁም ሌላው ፈርቶ አርፎ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ ነው።ብሎም ምንም አይነት እንቅሳሴ እንዳያሳይ ነው፡ ብላል።" የኢሰመጉን ቅርንጫፍ ለመክፈት በሞኮሩበትም የህወሓት ካደሬዎች እንደረበሸዋቸው ነበር ያስታወቁት።ከአምስት አመታት በፊት ይህ አይነት መልክ ይታይ በነበረበት ትግራይ ነው እንግዲህ አሁን እድሜ ላአንድነት ሃይሎች ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ የሚታየው። ለአራት አሰርት አመታት የተገነዘብነው ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ አብረው ለሚመጡ የአንድነት ሃይሎች የሚሰጠው ድጋፍ ቅጽበታዊና ፈጣን ነው።

ወታድሩና ሌላው የህብረተ-ሰቡ ክፍል አንድ ሆኖ በተነሳበት ወቅት ንጉሱን ለማውረድ ከባድ አለመኖሩ የሚታወስ ነው። በቀላሉ የተገኘ ለውጥ ስለነበረ ነው መሰል ያስከተለው መዘዝ ግን እስከ አሁንም ቢሆን ሊያባራ አልቻለም።ደርግም ቢሆን አጀማመሩ ላይ ሰፊ የህዝብ ድጋፍ የነበረው መሆኑን አሌ የሚባል ሃቅ አይሆንም። ኢህአፓና ሌሎች የአንድነት ሃይሎችም ቢሆኑ እንደዚሁ ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ የተቸራቸው ባጭር ጊዜ ውስጥ ባደረጉት እንቅስቃሴ ለመኖሩ በታሪክ መዛግብት የሰፈረ ነው፡፡ ከአምስት አመታት በፊት ቅንጅትና ህብረት የነበራቸው የህዝብ ድጋፍም ሲታይ እንደዚሁ ባጭር ጊዜ ውስጥ በተደረገው እንቅሰቃሴ ለመኖሩ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ይሁን እንጂ የአንድነት ሃይሎች በተለይም አመራሩ በፀና መንፈስና ብልህነት በተሞላበት አንድነቱን አስጠብቆ ዘለግ ላለ ጊዜ ሳይጉአዝ በመቅረቱ የኢትዮጵያ ህዝብ እስከአሁንም ቢሆን ነጻነቱን ሊቀዳጅ አልቻለም። እንዲያውም ለአንድነት ሃይሎች በሚያሳየው ድጋፍ የደረሰው ተደጋጋሚ ዘግናኝ ጥቃት ስናስታውስና አሁንም ቢሆን ግን ለለውጥ ያለው ፍላጎት ሳይገታ በትግሉ መቀጠሉ በጣም የሚደነቅ ነው።

የወቅቱ ያአንድነት ሃይሎች ተኪ ወይም ወራሽ ሆኖ ብቅ ያለው መድረክም በህዝቡ የሚሰጠው ድጋፍ እንደ ቀደምቱ ያአንድነት ድርጅቶች ከፍተኛ ነው።ይህ ሁሉ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራስያዊ ስርአት ለመገንባት ምን ያህል እንደጉአጉአ ነው።በተለይም የብርቱኩአንን አይነት ፅኑና መንፈሰ ጠንካራ መሪ በሚያገኝበት ጊዜ ህይወቱን ለመስጠት ወደኁኣላ የማይል ለመሆኑ በተደጋጋሚ አሳይታል። ቃልዋን ሳታጥፍ ለእወነት በፅናት በመቆሙዋም እንደስዋ ብዙ መንፈሰ ጠንካራና ጀግኖች ብቅ ብቅ እያሉ ነው።በአድዋ የነበለቱ ተወላጅ አቶ አረጋዊ ገ/ዮሃንስ አንዱ ናቸው።በድብደባ ብዛት በሞት አፋፍ ሆኖው በቪኦኤ ድምፃቸው ያሰሙት በአክሱም አውራጃ የውቅሮው ሰውና በአሩሲ ክፍለ ኀገር የአርባ ጉጉ አውራጃ ለፌዴራል ምክር ቤት እጩ ተወዳዳሪ የቅርብ ጊዜ የፅኑ ዜጎች ተምሳሌት ናቸው።

የእያሌ ጀግኞች ኢትዮጵያዉያን ስቃይና የፈሰሰው ደማቸው ግን የነፃነቱን ድል እያቃረበው ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይሆንም። ከኢትዮጵያውያን አልፎ የአለም ህብረተሰብ ሁሉ የህዝባችንን ግፍ ምን ያህል የከፋ ለመሆኑ በዝርዝር እያስተጋቡት ይገኛሉ። የሃገር ቤቱን የነጻ ሚዲያዎች መዝጋቱ አልበቃ ብሎ ቪኦኤ እንዳይደመጥ የኢትዮጵያ መንግስት ባፈነበት ማግስት ለሰው ልጆች ክብርና በሰላም መኖር የቆሙ Human Right Watch እና Amnesty International አለም አቀፍ ተቁአማት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እያሰሙ ነው።በመሆኑም የአመሪካውም ምክር ቤት በኢትዮጰያ ጉዳይ ውይይት ጀምሯል። የመለስ መንግስት አምባገነን መሆኑና ምርጫ ምርጫ የሚለውም ለመደለያና የግፍ አገዛዙን ለመቀጠል በመሳሪያነት የሚጠቀምበትን የጸጥታ ሃይሉን መመገብ የሚያስችለውን እርዳታ እንዳይቋአረጥበት ለማድረግ መሆኑን በትክክል ተገንዝበውታል። ስለሆነም መስዋእት የሆኑት ጀግኖቻችን ለተቀረው ውጤት እያስገኙለት ነው።የእውነት ክር ትመነምናለች እንጂ ኣትበጠስም ይባል የለ።Force Never disproves Truth! በሚል ርእስ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ከምርጫው በኋላ መጻፋቸውም አይዘነጋም።ያለፈውን ውሸት ለመሸፈን በሌላ ውሸት እየሞነቱ ምን ያህል ይዘለቅ ይሆን? ግማሽ መንገድ አልፈን ተቃዋሚዎችን እናስተናግዳቸዋለን፣እንቀበላቸዋለን፣ ጠንካራ ተቃዋሚ እኮ የአይንህን ጉድፍ መሳይ የምታይበት መስተዋት ነው እየተባለ የተፌዘት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ይሁን እንጂ ከግማሽ መንገድም ታልፎ ለሃገሪቱ የሚበጁ በህዝብ ፊት ሲነገር ሊዋጥላቸው አልቻለም። ከሃቅ ጋር ከተራራቁ ብዙ ጊዜ በማለፉ አሁን ድንገት ደርሰው ደግ ሰዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ በቀላሉ የምንረዳው ጉዳይ ነው። ይልቁንስ ያልሆኑትን ነን እያሉ የማያደርጉትን አደርጋልሁ እያሉ አሉባልታ በማስፋፋት ለብዙ ዜጎቻችን የህይወት ጠንቅ ለመፍጠር ሽርጉድ ማልቱ ማቆም ይኖሩባቸዋል ።በተጨማሪም በአቶ አረጋዊ ገ/ዮሃንስ የተፈጸመው አሰቃቂ ግድያና በሌሎች ንጹሃን ኢትዮጵያውያን በየቀኑ በመደረግ ላይ ያለዉ አረመንያዊ ድብደባዎች እስራቶችና ግድያዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማቆም አለባቸዉ እንላለን።

ግራም ነፈሰ ቀኝ ያለንበት ወቅት ባኣንጻራዊ መልኩ ሲታይ ለፍትህ ለቆሙት የኣንድነት ሃይሎች እያጋደለ በመምጣት ላይ በመሆኑ ሁኔታው የበለጠ ለወገንና የዲሞክራሲ ሃይሎች እየተመቻቸ እንዲሄድ ኣንድነታችንን ከምን ጊዜም ኣጠናክረን ወደፊት እንድንገፋ ጋሻ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ድል ለፍትህና ዲሞክራሲ ለቆሙት ያኣንድነት ሃይሎች!

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን

ሲያትል ዋሽንግተን

ኤፕሪል 03 2010 በፈረንጆች